# ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዝቅተኛዉ የደመወዝ ፖስተር

ይህ ማጠቃለያ ሰራተኞች ዝቅተኛውን የደመወዝ ተመን ዝርዝር እንዲያነቡ
በሚታይ ቦታ መቀመጥ አለበት

## ዝቅተኛ የክፍያ ዋጋዎች/በሰአት

| ጉርሻዎችን የማይቀበሉ ሰራተኞች | ጉርሻዎችን የሚቀበሉ ሰራተኞች |
|---|---|
| ከጁላይ 1፣ 2018 ጀምሮ በሰዓት $13.25 | ከጁላይ 1፣ 2018 ጀምሮ በሰዓት $3.89 |
| ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ በሰዓት $14.00 | ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ በሰዓት $4.45 |
| ከጁላይ 1፣ 2020 ጀምሮ በሰዓት $15.00 | ከጁላይ 1፣ 2020 ጀምሮ በሰዓት $5.00 |
| ከጁላይ 1፣ 2021 ጀምሮ በሰዓት $15.20 | ከጁላይ 1፣ 2021 ጀምሮ በሰዓት $5.05 |
| ከጁላይ 1፣ 2022 ጀምሮ በሰዓት $16.10 | ከጁላይ 1፣ 2022 ጀምሮ በሰዓት $5.35 |

ከ2021 ጀምሮ ጉርሻዎቸ ለማይቀበሉ እና ለሚቀበሉ ሰራተኞች በደንበኞች ዋጋ መረጃ ጠቋሚ መሰረት በእያንዳንዱ ተከታታይ ዓመት ዝቅተኛዉ ደመወዝ ይጨምራል። ዓመታዊ ዝቅተኛ የደመወዝ ተመኖችን በተመለከተ የቅጥር አገልግሎት መምሪያ ድህረ ገፅን በwww.does.dc.gov ላይ ይጎብኙ።

## የዝቅተኛ ደመወዝ ልዩ ሁኔታዎች

ዝቅተኛዉ የደመወዝ አቅርቦት ሌሎች ህጎች ወይም ደንቦች ለሚከተሉት ዝቅተኛዉ የደመወዝ ተመኖች በሚያዘጋጁበት ግዜ ተፈፃሚ አይሆንም:-

1. የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ዝቅተኛ ክፍያ ሊከፈላቸዉ የሚችለዉ አሰሪዉ ከ U.S. የሰራተኞች መምርያ የተፈቀደ የምስክር ወረቀት ሲደርሰዉ ብቻ ነዉ።
2. በስራ ፈጠራ እና በዕድል ሕግ ድንጋጌዎች ዉስጥ የተቀጠሩ ሰዎች በዚህ ህግ መሰረት ይከፈላሉ።
3. በወጣቶች የስራ ስምሪት ህግ ድንጋጌዎች የተቀጠሩ ሰዎች በዚህ ህግ መሰረት ይከፈላሉ።
4. እድሜያቸው በገፋ አሜሪካዉያን ህግ ድንጋጌዎች የተቀጠሩ ሰዎች በዚህ ህግ መሰረት ይከፈላሉ።
5. በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተቀጠሩ ተማሪዎች በአሜሪካ መንግስት የተቋቋመዉን ዝቅተኛ ደመወዝ ሊከፈላቸዉ ይችላል።
6. ከፌብሩዋሪ 26፣ 2015 ጀምሮ የወጣዉ የThe Wage Theft Prevention Amendment Act of 2014 ጎልማሳ ተማሪዎችን ከዝቅተኛ ደመወዝ ልዩ ሁኔታዎች አስወግዷል። ዕድሜያቸዉ 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አዲስ የተቀጠሩ ሰዎች በተቀጠሩበት ግዜ የተቋቋመዉን የኮሎምብያ ቀጠና ዝቅተኛ ደመወዝ ወድያዉኑ መከፈል አለባቸዉ።
7. ዝቅተኛዉ የደመወዝ ድንጋጌዎች በሚከተሉት ሰዎች ላይ አይፈፀምም:-
   a. በቅን ልቦና ስራ አስፈፃሚ፣ አስተዳዳራዊ፣ ባለሙያ፣ ኮምፒዉተር ወይም ከሽያጭ ዉጪ ባለዉ አቅም ዉስጥ የተቀጠረ ወይም
   b. ጋዜጦችን ወደ ሸማቹ ቤት በማድረስ ላይ የተሰማራ።

## የትርፍ ሰዓት ክፍያ

በስራ ሳምንት ከ40 ሰአታት በላይ ለተሰሩ ሰዓታት ቢያንስ 1 1/2 ጊዜ መደበኛ የክፍያ መጠን።

## የትርፍ ሰዓት ልዩ ሁኔታዎች

የትርፍ ሰዓት ድንጋጌዎች በሚከተሉት ላይ ለተቀጠሩ ሰዎች ተፈጻሚ አይሆንም:-

1. በቅን ልቦና ስራ አስፈፃሚ፣ አስተዳዳራዊ፣ ባለሙያ፣ ኮምፒዉተር ወይም ከሽያጭ ዉጪ ባለዉ አቅም ዉስጥ የተቀጠረ፤
2. በአሰሪዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ የሚኖር እንደ የግል የቤት ሰራተኛ የተቀጠረ፣
3. በችርቻሮ ወይም በአገልግሎት ማቋቋሚያ ዉስጥ የተቀጠረ እና መደበኛ የክፍያ ታሪፉ በህጉ መሰረት ከሚመለከተዉ ዝቅተኛ የሰዓት ክፍያ ከአንድ ተኩል ግዜ በላይ የሆነ እና ከግማሽ በላይ የሚሆነዉ የሰራተኛዉ ማካካሻ ለዉክልና ግዜ (ከአንድ ወር ያላነሰ) በሸቀጦች እና አገልግሎቶች ላይ ኮሚሽኖችን የሚወክል፣
4. እንደ የባህር ሰራተኛ፣ የባቡር ሃዲድ ሰራተኛ፣ በፓርኪንግ ወይም በፓርኪንግ ጋራጅ እንደ ረዳት ወይም በጋዜጣ ወደ ቤት ማድረስ የተቀጠረ፣
5. ለእነዚህ ሰራተኞች የሚሰጠዉን የአየር ጉዞ ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠቀም በፈቃደኝነት የስራ ቀናትን ከሌላ ሰራተኛ ጋር በሚለዋወጥ የአየር ጉዞ ተቀጥሮ የሚሰራ ወይም
6. እንደ ሻጭ፣ የክፍል ሻጭ፣ ወይም መካኒክ በዋናነት መኪኖችን፣ ተሳቢዎችን ወይም የጭነት መኪኖችን በመሸጥ ወይም በመከታተል ላይ የተሰማራዉ አምራች ባልሆነ ድርጅት ተቀጥሮ እነዚህን ተሽከርካሪዎች ለዋና ገዢዎች በመሸጥ ላይ ከተሰማራ።

ማስታወሻ:- ከሜይ 31፣ 2012 ጀምሮ የወጣዉ The Car Wash Employee Overtime Amendment Act of 2012 በመኪና እጥበት ሰራተኞች ላይ የነበረዉን የትርፍ ሰዓት ለዩ ሁኔታዎች አስውግዷል። የመኪና እጥበት ሰራተኞች ከአርባ ሰአት የስራ ሳምንት በላይ ለተሰሩ ሰዓቶች ሁሉ የትርፍ ሰዓት መብት አላቸዉ። ከኖቬምበር 12፣ 2015 ጀምሮ የሚሰራዉ የአሜሪካ የሰራተኛ የቤት ዉስጥ እንክብካቤ መምርያ ደንብ በኤጀንሲዎች እና በሌሎች የሶስተኛ ወገን አሰሪዎች የተቀጠሩ ቀጥተኛ የእንክብካቤ ሰራተኞች ተፈፃሚ ሆኗል። ቀጥተኛ የእንክብካቤ ሰራተኞች ማለት እንደ የተመሰከረላቸዉ የነርሲንግ ረዳቶች፣ የቤት ጤና ረዳቶች፣ የግል እንክብካቤ ረዳቶች፣ ተንከባካቢዎች እና አጋሮች ያሉ የቤት ዉስጥ እንክብካቤ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሰራተኞች ናቸዉ።

## በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ መሰረት የትርፍ ሰዓት የመከፈል መብት የሌላቸዉ ሰዎች በፌደራል ህግ መብት ሊኖራቸዉ ይችላል

ለበለጠ መረጃ ወደ U.S. የሰራተኞች መምርያ፣ የደመወዝ ሰአት ክፍል ይደዉሉ ወይም www.dol.gov/whd ይጎብኙ።

## የደንብ ልብሶች

አሰሪዎች በአሰሪ ወይም በህግ የሚጠየቁ የግዢ፣ የጥገና፣ የደንብ ወይም የመከላከያ ልብሶች ፅዳት ወጪዎች መክፈል አለባቸዉ ወይም ለሰራተኛዉ የሚታጠቡ የደንብ ልብሶች ከሚከፈለዉ ዝቅተኛዉ ደመወዝ (ቢበዛ የሚፈለገዉ በሳምንት $6.00 ነዉ) በተጨማሪ በሰዓት 15 ሳንቲም መክፈል አለባቸዉ። አሰሪዉ ሲገዛ እና ሰራተኛዉ የሚታጠብ የደንብ ልብስ ሲይዝ የሚፈለገዉ ተጨማሪ ክፍያ በሰዓት 10 ሳንቲም ነዉ። አሰሪዉ ሲያፀዳ እና ሲጠቅ ነገር ግን ሰራተኛዉ ሲገዛ የሚፈለገዉ ተጨማሪ ክፍያ በሰዓት 8 ሳንቲም ነዉ።

## ምግብ

አሰሪዎች ለእያንዳንዱ የቀረበ ምግብ $2.12 ሊቀንሱ ይችላሉ። ለአራት (4) ሰዓታት ወይም ከዚያ ላነሰ ስራ ቢበዛ አንድ (1) የምግብ ቅነሳ ይፈቀዳል። ከአራት (4) ሰዓታት በላይ ለሚሰራ ስራ ቢበዛ ሁለት (2) የምግብ ቅነሳ ይፈቀዳል። በአሰሪዉ ግቢ ዉስጥ ለሚኖሩ ሰራተኞች በቀን ከ $6.36 በላይ ሊቀነስ አይችልም።

## ሌሎች ድንጋጌዎች

ተጨማሪ ደመወዝ በሰራተኞች ምክንያት ለሚኖሩ የተከፋፈለ ፈረቃ፣ የጉዞ ወጪዎች እና ለመሳርያዎች ነዉ። በአሰሪዉ ለተሰጡ ማረፍያዎች ሌሎች ተቀናሾች ሊወሰዱ ይችላሉ።

## ተቀናሾች

ማንኛዉም አሰሪ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካልተፈቀደ በስተቀር ደመወዙን በህጉ ከሚጠየቀዉ በታች የሚያደርጉ ምንም ዓይነት ተቀናሽ ማድረግ የለበትም። ሁሉንም ተቀናሾች የሚያሳይ የደመወዝ መግለጫ ለእያንዳንዱ የክፍያ ቼክ መቅረብ አለበት።

## መዝገቦች

ማንኛዉም አሰሪ ቢያነስ ለሶስት (3) ዓመታት ትክክለኛ ግዜ እና የክፍያ መዝገቦች ለእያንዳንዱ ሰራተኛ በህጉ ከሚያስፈልጉት ሌሎች ዝርዝር መዝገቦች በተጨማሪ ያስቀምጣል።

## ጉርሻ የሚሰጣቸዉ ሰራተኞች

አሰሪዎች "ጉርሻ ለሚሰጣቸዉ ሰራተኞች" የአገልግሎት ዋጋ በሰዓት (እባክዎ በዚህ ሰነድ ዉስጥ ጉርሻ በሚሰጣቸዉ ሰራተኞች ስር በተደነገገዉ ደንብ አሁን ያለዉን የዝቅተኛ ክፍያ መጠን ይመልከቱ) መክፈል አለባቸዉ። የሰራተኛዉ የሰዓት ጉርሻ ገቢ (በአማካኝ በየሳምንቱ) በአገልግሎቱ መጠን ላይ ተጨምሮ ከዝቅተኛዉ ደመወዝ ጋር እኩል ካልሆነ አሰሪዉ ልዩነቱን መክፈል አለበት።

## የሩብ ዓመት ደመወዝ ዘገባ በኦንላይን ሪፖርት ለማድረግ በይነመረብ ላይ የተመሰረተ የጉርሻ ፖርታል

ጉርሻ የሚቀበል ሰራተኛን የሚቀጥር አሰሪ ሰራተኛዉ የሚፈለገዉን ዝቅተኛ ደመወዝ መከፈሉን የሚያረጋግጥ
እያንዳንዱ ሩብ ዓመት ካለቀ በ30 ቀናት ዉስጥ የሩብ ዓመታዊ የደመወዝ ሪፖርት ለከንቲባዉ ማቅረብ አለበት።

1. ከንቲባዉ በ https://www.essp.does.dc.gov/ ላይ የሚገኝ የሩብ ዓመት ደመወዝ ዘገባ በመስመር ላይ ሪፖርት ለማድረግ በይነመረብ ላይ የተመሰረተ ፖርታል ፈጥሯል።
2. አሰሪዉ በመስመር ላይ ሪፖርት ማድረግ ችግር ይፈጥራል ብሎ ካልተናገረ በስተቀር አሰሪዉ የሩብ ዓመት የደመወዝ ሪፖርቱን በኦንላይን ማቅረብ አለበት፤ ችግር የሚፈጥር ከሆነ አሰሪዉ ሪፖርቱን በደረቅ ቅጅ ማቀረብ አለበት።
3. ከንቲባዉ ለአሰሪዎች ስለ ሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች እና በበይነ መረብ ላይ የተመሰረተ ፖርታል አጠቃቀምን ለማስተማር የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን ስልጠና ይሰጣል።

## በደመወዝ-ሰዓት ቢሮ የሚተዳደሩ ተጨማሪ ህጎች

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዉስጥ የሚተገበሩ ሁሉም የሰራተኛ ህጎችን በ www.does.dc.gov ላይ ማግኘት ይችላል።

## ለእያንዳንዱ ህግ ሙሉ ፅሑፍ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ የሚከተለዉን ያግኙ


**የቅጥር አገልግሎቶች መምርያ የደመወዝ ሰዓት ቢሮ**
4058 MINNESOTA AVENUE, N.E.
Washington, D.C. 20019
(202) 671-1880 | www.does.dc.gov